# የሕይወት መንገድ

ከፖፕ ሺኖዳ ሣልሳዊ

ትርጉም፡- በሰሎሞን በቀለ

ሚያዝያ 1994 ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

አይደለም። ይሁን እንጂ ብስለት ያለው ሰው ዝምታን ይመርጣል ብንል ያስኬዳል።

ብስለትን በተመለከተ አንድ ታላቅ መንፈሳዊ አባት የተጠቀሙትን ምሳሌ ላቅርብልዎ።

ምሳሌውም እነሆ እግዚአብሔር ወደ ሕይወት ባሕር ውስጥ እንደጠጠር በወረወረኝ ጊዜ በሕይወት ባሕሩ የላይኛው ገጽታ ላይ አረፋዎችን ፈጠርኩ አረፋዎቹም ክቦችን፣ ክቦቹም ትንሽ ሞገድን ፈጠሩና ባሕሩ ተናወጠ፣ ወደታችኛው የባሕር ወለል በደረስኩ ጊዜ እንደ ልቤ መሆን ስለቻልኩ ተረጋጋሁ።

በዚህን ወቅት ማዕበል፣ ሞገድና ሁከት የነበረው በባሕሩ የላይኛው ገጽታ እንጂ የታችኛው የባሕር ወለል ላይ አልነበረም። የታችኛው የባሕር ወለልማ ያለመናወጥ ጸጥ ያለ ነው።

የሰው የኑሮ ሂደትም ልክ እንደዚሁ ነው። ማንኛውም ሰው ገና ሕላዌውን አንድ ብሎ ሲጀምር እና እራሱንም የመኖር ያለመኖር የማንነት ጥያቄ ሲጠይቅ በመነሻው የውጣ ውረድ አረፋዎችን መፍጠሩ አይቀሬ ነው። እኚህም አረፋዎች በሕይወት ጅምር ላይ ያለምንም ማቋረጥ መኖራቸውም ሀቅ ነው። ቢሆንም ይህ ሰው ከሕይወት ልምዱና ተሞክሮው ብዙ ሲማር በእድሜውም ሲጎለምስና ሁኔታዎችን ሁሉ ከየአቅጣጫው ማመዛዘን ሲችል ፍጹም የተረጋጋና ብስለት ያለው ይሆናል። የሕይወት ልምድና ተሞክሮ የሌለው ግን ሁል ጊዜ በኑሮው ተሸናፊ ስለሆነ ይጨነቃል። ተሸናፊ ሰው ብስለት



የሌለው ሲሆን ራሱንም ወዳድ ከመሆኑ የተነሳ ይታወካል ሥጋዊ ምኞቱንም ለማሳካት ላይ ታች እያለ ሲባትል ተቅበዝባዥ ይሆናል እንጂ አይሳካለትም።

ከላይ እንደተገለጸው በዕድሜም ሆነ በዕውቀት በሳል መሆን የተረጋጋ ኑሮን ለመኖር በጣም እንደሚጠቅም ማወቅ አያዳግተንም።

## ዕውቀት

በዚህ ርዕስ ሥር የብስለትን እና የዕውቀትን ልዩነት እንዲሁም ከዝምታ እና ከእርጋታ ጋር ያላቸውን ዝምድና አብራራለሁ። በገሀዱ ዓለም የምርምር ተሰጥኦ እና ትምህርታዊ ዕውቀት ያላቸው ብዙ ምሁራን አሉ።

ስለእነዚህ ምሁራን ትምህርታዊ ዕውቀት እና የምርምር ተሰጥኦ "ብዙ ሰዎች ይመረምራሉ ዕውቀትም ይበዛል" ተብሎ ትንቢት ተነግሯል (ት.ዳን. 12፥4)። ትንቢቱም ትምህርታዊ ዕውቀታቸው ከጊዜ በኋላ ከሌላ ሰው፣ ከቤተሰብ፣ ከት/ቤት ከተፈጥሮ ወዘተ እንዳገኙት ይጠቁማል።

በዚህም የሰው ልጅ በባሕር፣ በዕጽዋት፣ በእንስሳት እና በግዑዛን ፍጥረታት ላይ ያለው ጠቅላላ ዕውቀት እና ምርምር ዓለምን ሲጠቅም ይታያል። ነገር ግን ይህ ዕውቀት ፍጹም መንፈሳዊነት ካልታከለበት ዓለምንም ሊጎዳ ይችላል።



www.ethiopianorthodox.org

ሰላም በጽሞና እንደሆነ ይገንዘቡ። እግዚአብሔር በራሱ የጊዜ ቀመር እና በራሱ ፈቃድ ተአምራትን ይከስታል እንጂ ሰዎች ምልክት ለማየት ፈልገው ስለጠየቁት ብቻ ወይም ያላመኑትን ለማሳመን ብቻ ተአምራት አያደርግም። ምክንያቱም ተአምር እምነትን የምንፈበርክበት መሳሪያ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ጌትነቱን እና መለኮታዊነት የምንረዳበት ኃይል ነው። የእግዚአብሔርን አምላክነት የሚያምኑ፣ ተአምራት የጌትነቱ መገለጫ እንደሆነ ይቀበላሉ፣ ከዚያም ከተአምራቱ ለሕይወታቸው መልካም አቅጣጫን የሚቀይሱበትን የእግዚአብሔር ሐሳብ ይረዳሉ።

ነባቤ መለኮት ዮሐንስ "ኢየሱስ ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም እራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል" ብሎ እንደጻፈልን (ዮሐ. 21፥25)። ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም እና ከጻድቁ ከዮሴፍ ጋር ወደ ግብጽ ሀገር በተሰደዱ ጊዜ የተከሰቱት ብዙ ምስጢራዊ ተአምራት እንደ ምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ብዙዎቻችን ከእነዚህ ተአምራት መካከል የምናውቃቸው ግን በወንጌላት እና በአዋልደ መጻሕፍት የሰፈሩትን ጥቂቶቹን ብቻ ነው።

በዚህ ዓለም በእግዚአብሔር ፊንታ እንጨት ጠርበው ድንጋይ አለዝበው ጣዖትን የሚያመልኩ አሉ። ይሁን እንጂ በጣዖት አምላኪዎች ላይ ከእግዚአብሔር የተቃጣ መቅሰፍት ከሰማይ ሰራዊትም የተነሳ



ተቃውሞ የለም ወይም እግዚአብሔር እነርሱን ለማጥፋት ከሰማይ እሳት አላዘነበም።

ሌሎች ደግሞ የእራሳቸውን ምናባዊ ፍልስፍና ተከትለው እግዚአብሔር የለም በማለት በእግዚአብሔር ላይ የስድብን ቃል ይሰነዝራሉ። አሁንም ድረስ በኃጢአታቸው ውስጥ የራሳቸውን ኑሮ ይኖራሉ እንጂ እግዚአብሔር ከቸርነቱ ብዛት ሁሉም እርሱን እስኪያውቁት ድረስ ዝምታን መርጧል። ይህም እግዚአብሔር የለም በሚሉት ፊት የእግዚአብሔር ዝምታ ፍጹም የሚያስደምም ነው።

ምክንያቱም ሰዎች የተሰጣቸውን ዕውቀት እና ነጻ ፈቃድ ተጠቅመው አሁንም ያለንበት ዘመን ድረስ እግዚአብሔርን ቢቃወሙም እግዚአብሔር ግን አሁን ዘመኑ የምሕረትና የይቅርታ ስለሆነ እጅ በእጅ በኃጢአታቸው ሊቀጣቸው አልፈለገም። ሁሉንም እስከ መጨረሻም የፍርድ ቀን ድረስ ይታገሳቸዋል። በተጨማሪም ከኃጢአታቸው እንዲነጹ ዘመን ለፍስሐ የሰጣቸውን ያህል ዕድሜ ለንስሐ ሰጥቶ ንስሐ እንዲገቡ ወደ እርሱ የመመለስ አጋጣሚዎችን እየፈጠረላቸው ነው።

ከዚህ በላይ የሚያስደንቀን የእግዚአብሔር ቸርነት ደግሞ ቅዱስ ማቴዎስም "እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና በጻድቃን እና በኃጢአተኞች ላይ ዝናቡን ያዘንባልና" (ማቴ. 5፥45) ሲል ስለ እግዚአብሔር ቸርነት እንዳብራራው ኃጢአተኞች እና እግዚአብሔር የለም ባዮች አመጸኞች ምንም እንኳን ለእግዚአብሔር



www.ethiopianorthodox.org

ለምሳሌ የቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ባለበት ቦታ ሁሉ እና ስሙ በተጠራበት ቦታ ቅዱስ ገብርኤል ይገኛል። ስለ መላእክት ይህን ያህል አብራራን እንጂ ቅዱሳንም በአጸደ ነፍስ ያላቸው ጸጋ እና አገልግሎት እንደ መላእክቱ ነው።



# ምዕራፍ ሁለት

## ዝምታ ዓይነቶቹ እና መገለጫዎቹ

ዝምታ ውጫዊውንም ሆነ ውስጣዊውን፣ የሚታየውንም ሆነ የማይታየውን የሰውን ማንነት መግዛት የሚችል ኃይል ነው። የሚታይ እና የማይታይ የሰው ማንነት ስንል ምን ማለታችን ነው። ይህም የሚከተሉትን ንዑስ ርዕሶች ያካትታል።

1. ዝምታ ውስጣዊ ሰላም ነው፤ ይህም ከአዕምሮ ዕረፍት፣ ከመንፈስ መረጋጋት እና ከህሊና ሰላም ይመጣል።

2. ዝምታ የሰውነት መረጋጋትን እና የስሜት ሕዋሳት ስክነትን (እንቅስቃሴን) ያካተተ አካላዊ አደብ ነው።

3. ዝምታ የደስታ መንፈስን ከፊት ፈገግታ ጋር የሚያቆራኝ ስሜታዊ እርጋታ ነው።

4. ዝምታ አንደበትን መግታት ነው፤ ይህም በንግግር ጊዜ የድምጽ ቀላጤን እና ለዛን ሲያካትት በዝምታ ጊዜ ደግሞ የውስጥ ስሜትን ይቆጣጠራል።

5. ዝምታ በኑሮ ውጣ ውረድ እና በግል ባሕርይ ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን እና ተለዋዋጭ ገጠመኞችን የምንጋፈጥበት ስልት ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ልክ እንደ ዐይነ ስውሩ ቅ.ደዲሞስ በኑሮው የተረጋጋ እና በማንኛውም ውይይት እና ክርክር ውጤታማ ለመሆን የማይመጥ ልምድ ያስፈልጋል።

ዐይነ ስውሩ ዲዲሞስ በአንድ ወቅት ሐልዎተ እግዚአብሔርን የሚክዱ ተመራማሪዎች የራሳቸውን ዕውቀት ማስረጃ በማድረግ የእግዚአብሔርን አለመኖር ከነገሩት በኋላ እስኪ አንተ እግዚአብሔር መኖሩን በተጨባጭ አስረዳን ሲሉ ጠየቁት። እዚህ ላይ ዲዲሞስ ተመራማሪዎቹ ጭልጥ ብለው መሳሳታቸውን ቢያውቅም ንግግራቸውን እስኪጨርሱ በጥሞና ያዳምጣቸው ነበር እንጂ አልተበሳጨም። ሐሳባቸውንም ከተረዳ በኋላ ለጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ምሽት ተመልሳችሁ ኑ አላቸው። እነርሱም የቀጠሮአቸውን ጊዜ አክብረው ሲመሽ ተመልሰው መጡ።

ዲዲሞስም እንግዲህ አሁን እስኪ ወደላይ አንጋጣችሁ የሰማዩን ገጽታ ተመልከቱ አላቸው እነርሱም እንዳላቸው ሰማዩን ተመለከቱ። እርሱም "በሰማይ ላይ ምን እና ምን ይታዩአችኋል" አላቸው።

እነርሱም፡- "ከዋክብት" ብለው መለሱለት

እርሱም፡- "በሥጋዊ ዐይናችሁ የማየት ችሎታ እነዚህን ከዋክብት በቀን ማየት ትችላላችሁን?" ሲል ጠየቃቸው

እነርሱም "አንችልም" አሉ

እርሱም "ለምን ማየት ያቅታችኋል" ሲል ጥያቄውን በጥያቄ ደገመላቸው

እነርሱም "ከዋክብቱን ለማየት የግድ መምሸት አለበት" አሉት።



እርሱም "በእርግጥ ትክክል ናችሁ የመለሳችሁት ምላሽ ትክክል ነው፤ ይሁን እንጂ በተፈጥሮ እንደምናውቀው የተሰወረን ነገር ለማግኘት ብርሃን ያስፈልጋል እነዚህን የምታዩአቸውን ከዋክብት ለማየት ግን ብርሃን ሳይሆን ጨለማ ሊኖር የግድ ነው። እንደዚሁ ሁሉ እግዚአብሔርንም ለማየት ቁሳዊ ነገርን ማየት በሚቻልበት በሳይንስ መሣሪያ እና ፍልስፍና ሳይሆን በእምነት ብቻ ማረጋገጥ እንደሚቻል ልነግራችሁ እወዳለሁ" በማለት አስረዳቸው።

ከዚያም እርሱ በተራው በሰማያት ገጽታ ላይ ከዋክብት እንደሚታዩ ነግራችሁኛል። ይሁን እንጂ እኔ ዓይነ ስውር ስለሆንኩ በምን ታረጋግጡልኛላችሁ ሲል አዲስ የጥያቄ ርዕስ ከፈተላቸው። እነርሱም ግራ ተጋብተው ምላሽ አጡ እና ከመናገር ይልቅ ዝምታን መረጡ።

እርሱ ግን የእኔ ዐይነ ስውርነት የከዋክብቱን አለመኖር አያረጋግጥም እኔ አየሁም አላየሁም ከዋክብቱ ዘወትር አሉ። እኔም ምንም ዐይነ ስውር ብሆንም እንኳን ከዋክብቱን ሳልመለከት እናንተ አይታችሁ በነገራችሁኝ ምስክርነት ብቻ የከዋክብቱን መኖር አምኜ ተቀብዬአለሁ አላቸው። እኔ አንዳች ከዋክብት ሳልመለከት የከዋክብቱን መኖር እንዳመንኩ እናንተም በሥጋዊ ዓይናችሁ ባትመለከቱትም እንኳ በእምነት እግዚአብሔር መኖሩን አታምኑምን? ብታምኑ መልካም ነው ሲል በትሕትና ጠየቃቸው።



www.ethiopianorthodox.org

ያስጨርሳል። በውይይቱ እና በክርክሩም ምንም ዓይነት የሽንፈት እና የበታችነት ስሜት ሳይሰማው በሐሳቡ እንዲስማሙ ስለሚያደርገው ይረቱለታል።

የመደማመጥ ልምድ የሌላቸው ሰዎች ሁሉ በውይይታቸው ጊዜ ስለማይደማመጡ እያንዳንዳቸው ቢያንስ ቢያንስ አንድም አምስትም ናቸው ሁሉም ስለማያወሩ እና ስለማይደማመጡ ወደ መግባባት አይመጡም።

የመደማመጥ ልምድ ያላቸው ሰዎች ግን በአንድ ውይይት ውስጥ ከመቶ በላይ እንኳን ቢሆኑ ምንም አይነት የጩኸት እና የጫጫታ ድምጽ አይሰማዎትም።

በመሠረቱ ሁላችንም በውይይት እናበክርክር ጊዜ የየራሳችን ሐሳብ ትክክል እና ቅዱስ ቢመስለንም እንኳን መደማመጥ ካለ የማይጣጣሙ ሐሳቦችን በማንሸራሸር ወደ አንድ እውነት ነው መድረስ እንችላለን።

*ስለዚህ ሰዎችን ላለማጣት፣*
*የተረጋጋ ኑሮ ለመኖር፣*
*ወደ እውነት ለመምጣት*
*የማድመጥ ልምድ ይኑረን።*



## ለ) ትክክለኛ ሒስ

ስለ መደማመጥ እና ስለመወያየት ከተነጋገርን አሁን ደግሞ ስለሒስ መነጋገር አለብን። ትክክለኛ ሒስ ከልብ የመነጨ ልባዊ ምክር ሲሆን የእውነት እና የፍቅር መገለጫ ነው። ትክክለኛ ያልሆነ ሒስ ግን ነቀፋ ወይንም ትችት ሲሆን የቅናት እና የምቀኝነት ስሜትን ያንጸባርቃል። ትክክል ያልሆነ ሒስ ጠብን እና መከፋፈልን የሚያባብስ ሲሆን ትክክለኛ ሒስ ግን ሁሉንም ሰው ወደ ሰላም እና መፍትሔ የሚያመጣ ነው። ትክክለኛ ሒስ ሰዎች ጥፋታቸውን በተዘዋዋሪ መልኩ እንዲረዱት የሚያደርግ ኃይል ነው።

ትክክለኛ ሒስ የሰላማዊ ሰው መለያ ምልክቱ ነው። ምክንያቱም ሰላማዊ ሰው ዘወትር ሰዎች በስሕተታቸው እንዳይጠፉ ትክክለኛ ሒስ ይሰነዝርላቸዋል። አትኩሮቱም ስሕተትን ከመፈለግ ይልቅ መፍትሔን ወደማምጣት ነው። ሰው ስሕተት ሲሰራ ቢያጋጥመው እንኳን ይህን አታድርግ ይህንን አትሥራ ጳግመኛ እንዲህ አትሁን ብሎ ሲያዝ አይሰማም ነገር ግን በሌላ አገላለጽ ይህ ጉዳይ የሚሆን ይመስልሃል። "...እንዲህ ብታደርግ ይስማማሃል?" በማለት በጥያቄ መልኩ ሐሳቡን ያቀርባል። ሁሉም ሰው በነጻነት እንዲኖር ይፈቅዳል። ከበታቹ የሚሠሩ ረዳቶችንም ቢሆን አድርጉ አታድርጉ በሚል ደረቅ ሕግና ትእዛዝዝ አያታክታቸውም። ፍላጎቱ ሰዎች በስሕተታቸው እንዲጠፉ ሳይሆን ከስሕታቸው እንዲማሩና እንዲሻሻሉ ማድረግ ብቻ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ለሰው ዘር በሙሉ በሕዋሳዊ አገልግሎት ሥር መሆን በጣም ቀላል ስለሆነ ሰው በሚያየው፣ በሚያሸተው፣ በሚነካው . . . ነገር አማካይነት በቀላሉ ይሳባል፤ ከዚያም ይታወካል። በሕዋሳቶቻችን አማካይነት እንዳንታወክ ሕዋሳዊ ስክነትን በተመለከተ ገዳማውያን አበው "ወደ ወንድምህ ቤት በገባህ ጊዜ እዚያ እና እዚህ እያማተርክ አትመልከት፤ በማዕድም ላይ ስትቀመጥ እንኳን ፊትህ የቀረበውን ተመገብ እንጂ ዐይኖችህን ወዲያና ወዲህ እያቅበዘበዝክ አትቀላውጥ" ሲሉ ይገስጻሉ።

አበው የስሜት ሕዋሳትን ተጠቅሞ የሌሎችን ምሥጢር ማወቅ እና ገበናን መመልከት በራሱ "ሕዋሳዊ ዝሙት" ይሉታል። ጆሮ ማድመጥ የሌለበትን ነገር ሲያዳምጥ "የጆሮ ዝሙት" ይባላል። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ የጆሮ አጠቃቀም በሥውር ከማድመጥ አይለይምና።

ዐይንም ማየት የማይገባውን አጮልቆ ወይም አማትሮ ሲመለከት "የዐይን ዝሙት" ይባላል። የሌሎቹም ሕዋሳቶች ክንዋኔ እንዲሁ አለ አግባብ ከሆነ ይህንን ስያሜ ያገኙታል ለዚህ ዓይነቱ ሕዋሳዊ ዝሙት ወይም ክንዋኔ ተጠቂ መሆን ደግሞ እንደሰይጣን ቅናትን ተላብሶ ለጥፋት መሰለፍ ማለት ነው። "ሰይጣንም በምድር ላይ ዞርሁ በእርስዎም ተመላለስሁ ብሎ መለሰ" (ኢዮብ 2፥2)።



ስለዚህ ሁላችንም በስሜት ሕዋሳቶቻችን አማካይነት እንዳንታወክ እና ለጥፋት እንዳንሰለፍ "ከሕዋሳዊ ዝሙት" መታቀብ አለብን።

## ፈገግታ

ፈገግታ በፊት ገጽታችን አማካይነት ውስጣዊ ሰላም እና ደስታ የሚታወቅበት የመረጋጋት ዓይነት (ምልክት) ነው። ይህም ከውስጥ የመነጨውን ፈገግታ እንጂ ሰው ሠራሽ የሆነው የለበጣ ፈገግታ ማለታችን አይደለም።

የፊት ገጽታችን ወይንም ዓይን ውሃችን የውስጥ ስሜታችን የሚንጸባረቅበት መስታወት እና በህሊናችን የሚመላለሱት ሐሳቦች የሚነበቡበት ሰሌዳ ነው። ይህም መወደዳችን፣ ጥላቻችን፣ ሀዘናችን፣ ደስታችን፣ ፍርሃታችን፣ ድፍረታችን፣ የውስጥ ስሜታችን ሁሉ በፊት ገጽታችን እንደሚታወቅ ያስረዳናል።

አንዳንድ ሰዎች ውስጣቸው ሲረበሽ ወይም ወንጀል ለመሥራት ሲፈልጉ የውስጥ ሐሳባቸው እና ስሜታቸው እንዳይታወቅ ለዐይናቸው ጥቁር መነጽር እና ለፊት ገጽታቸው ቅባት ይጠቀማሉ፣ ወይም ለዐ ይናቸው መነጽር ለፊታቸው ቅባት ባይጠቀሙ እንኳን ውስጣዊ ፍርሃታቸው፣ ጭንቀታቸው እና አለመረጋጋታቸው እንዳይታወቅባቸው ብዙ ይጥራሉ።



www.ethiopianorthodox.org

በአንድ ወቅት አንዲት ጸሐፊት በአንድ የሠርግ የእራት ግብዣ ላይ ከአለቃዋ ጋር በርቀት ይተያያሉ ይሁን እንጂ አጋጣሚዎችን ተጠቅማ ለአለቃዋ ሰላምታ ማቅረብ ስትችል አላቀረበችም። በዚህም አሁን ምን ይለኛል በሚል ሐሳብ ግራ ተጋብታለች። ይህ በእንዲህ እንዳለ የሠርጉ የእራት ግብዣ ተጠናቆ ሁሉም እድምተኛ ወደየቤቱ ሲያቀና ደግሞ ብዙ ትርምስ ሳለ ይህች ሴት እንደ ድንገት ያስነጥሳታል በምታስነጥስበትም ጊዜ ከአፍንጫዋ የተወናጨፈው ምራቅ መሰል ከአለቃዋ ጫማ ላይ ያርፋል፣ አለቃዋ ግን ሲያስነጥሳት አልሰማትም፣ ምራቅ መሰሉንም ከጫማው ላይ ሲወድቅ አልተመለከተም።

ዳሩ ግን ይህቺ ሴት በመጀመሪያ በእራት ግብዥው ላይ አይታው ሰላም አለማለቷ እያሳሰባት ሳለ ዳግመኛ ይህ ሁኔታ በአጋጣሚ መፈጠሩ በይበልጥ ረበሻት

*አሁን እኮ አውቄ የተፋሁበት ይመስለዋል የናቅሁትም ሊመስለው ይችላል አልያም ከባላጋራዎቹ ከእነ እገሌ ጋር ተባባሪ ያደርገኛል በዚህም ሳቢያ ከሥራዬም ሊያባርረኝ ይችላል ታዲያ ምን ባደርግ ይሻለኛል?* በማለት ሳታውቅ የሠራችውን ስሕተት እያጋነነች እና ሆን ብላ እንደሰራችው እራሷን እያሳመነች ጭንቀት ውስጥ ገብታለች። በአጋጣሚ የተፈጠረውን ስሕተቷን ማጋነኗ ሳትወድ በግድ የአዕምሮ መባከንን እና ስሜታዊ መታወክን አስከተለባት።



የዚች ሴት ችግር የብዙዎቻችን የጋራ ችግር እንጂ የእርሷ ብቻ አይደለም። ብዙውን ጊዜ ሁላችንም አውቀን በድፍረት ሳናውቅም በስሕተት የምንፈጽመው ድርጊት ይኖራል ታዲያ ያደረግነው ድርጊት ስሕተት ከማይዛመዱ እና ከማይመሳሰሉ ሁኔታዎች ጋር እያቀራረቡ ማ ማን ሳይሆን ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተውን ክፍል ወዲያው ይቅርታ መጠየቅ ብቻ ነው። ከይቅርታ በኋላም እራሳችንን ማረጋጋት ያሻናል።

➢ ***ክፉ ሐሳብ***

ታላቁ እንግሊዛዊው ሊቅ ዊልያም ሼክስፒር "ምንም ነገር መጥፎም ጥሩም ሊሆን ይችላል ለአንድ ነገር ከሁለቱ አንዱን ትርጉም ሊያሰጠን የሚችለው አስተሳሰባችን ነው" እንዳለ።

በዓለማችን ላይ ሁለት ዓይነት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች አሉ። የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ሰናይ ራዕይ ስላላቸው የሁኔታዎች ሁሉ መልካም ውጤት ይታያቸዋል። እነዚህ ሰዎች በችግሮቻቸው እና በመከራቸው ጊዜ እንኳን ትክክለኛ መፍትሔ ያገኛሉ።

ሌሎቹ ዓይነት ሰዎች ደግሞ ዓሉታዊ አስተሳሰብ ስላላቸው የሁኔታዎች ሁሉ መጥፎ ገጽታ ይታያቸዋል። በዓለማችን በዚህ አሉታዊ ክፉ ሐሳብ አያሌዎች ይጠቃሉ፤ መሠረት በሌለው ፍርሃት እና ስጋት ይሰቃያሉ፤ ከዚህም የተነሣ ብዙ ሥነ-ሥርዓታዊ ድርጊቶችን ያከናውናሉ። ከሚያከናውኗቸው ድርጊቶች መካከል ጀርሞችን ለማስወገድ ከሚገባው በላይ ደጋግሞ እጅን መታጠብ፣ የተናገሯቸውን



www.ethiopianorthodox.org

ረቡዕ እና አርብ አይሆኑኝም ምን ይሻለኛል? ቀኝ እግሬን እንቅፋት መታኝ አይቀናኝም የመሳሰሉትን ጎጂ ልማዶችን በመቀበል ሰው መሠረት በሌለው ፍርሃት የሚሠቃይበት አስተሳሰብ ነው።

ስለዚህ መጥፎ ልማድ፣ የቤት ጣጣ እና አጉል ባሕል ያላቸው ሁሉ የጽልመታዊ አመለካከት ተከታዮች ስለሆኑ እኛቸውን ለሰይጣን የሰጡ ምርኮኞች ናቸው። ከዚህም የተነሣ

1ኛ) የአጉል እምነት ተገዥዎች ይሆናሉ፤

2ኛ) ለተመሳሳይ የውርስ በሽታ ይጋለጣሉ፤

3ኛ) በጥንቆላዊ ምት ይቀሰፋሉ፤

## *1ኛ) <u>የአጉል እምነት ተገዥዎች</u>*

በጽልመታዊ አመለካከት አማካይነት የሚመጣ አጉል እምነት ተምረዋል የምንላቸውን ሰዎችን ሳይቀር ያጠቃል።

እነዚህም ሰዎች እንደ ዐውደ-ነገሥት ያሉ የኮከብ ቆጠራ (Astrology) ጋዜጦችን እና መጽሔቶችን በተለይ ስለ ጠባያቸው እና ባሕርያቸው የሚናገረውን የኮከብ ክፍል በማየት እና በማንበብ ይታወካሉ።

በመሠረቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ በስተቀር ስለ ሰው ነገንትና ዛሬነት የሚናገር እንዲሁም የወደፊት ዕድል - ፈንታን የሚተነብይ መጽሐፍም ሆነ አንዳች ቁሳቁስ የለም።



ለሰው ዘር የሕይወት መዝገበ ቃላት መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ እንደሆነ ማመን ይገባል። ማንኛውም የቋንቋ መዝገበ ቃላት አንድን ግስ (አንቀጽ) በተለያየ ዓይነት መልኩ እንደሚፈታ ግልጽ ነው። ለምሳሌ የአመርኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት በላ የሚለውን ግስ

1. ተመገበ
2. አላመጠ/አኘከ
3. ነከሰ (ውሻ እንዳይበላህ ተጠንቀቅ)
4. አሳከከ/ቆጠቆጠ
5. አሸነፈ/ረታ/ገቢ አገኘ (ለቁማር)
6. ጨረሰ/ፈጀ (መኪናዋ ቤንዚል ትበላለች)
7. ተቀበለ/ወሰደ (ካሳ በላ)
8. አቃጠለ/ፈጀ (እሳት በላው) እያለ እንደየአገባቡ በተለያየ ዓይነት ይተነትነዋል።

እንደዚሁ ሁሉ የሕይወት መዝገበ-ቃላት የሆነው መጽሐፍ ቅዱስም ስለጋብቻ፣ ስለ ምንኩስና፣ ስለ ኑሮ፣ ስለ ደስታ፣ ስለጭንቀት በጥቅሉ ሰው ማወቅ ስለሚያስፈልገው ነገር ሁሉ የራሱ የሆነ መለኮታዊ ትንታኔ አለው።

መጽሐፍ ቅዱስ ለችግር የእግዚአብሔር መፍትሔ፣ ለሥጋዊም ሆነ ለመንፈሳዊ ጥያቄዎች የእግዚአብሔር መልስ ነው። ፊደል የቆጠሩ ሰዎች በዚህ ዓለም ዕድል ፈንታቸውን ለማወቅና የሚመጣውንም ዓለም ዘላለማዊነት ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እንጂ እንደ



www.ethiopianorthodox.org

ምክንያቱም እነርሱን ድል ለመንሳት በቂ ኃይል አለን" በማለት እምነታቸውን ሲገልጹ (ዘኍ. 13፥30)።

የተቀሩት ዐሥሮቹ ሰላዮች ግን በምናባዊ ፍርሃት እየተንቀጠቀጡ እና እየተብረከረኩ "እኛ በእነርሱ ላይ አደጋ ለመጣል ከቶ በዚያ የሚኖሩት ሕዝብ ከእኛ ይበልጥ ብርቱዎች ናቸው። ቁመተ ረጃጅሞች የሆኑ ጦረኞች ናቸው። በዚያም ግዙፋን የሆኑትን የዔናቅን ዝርያዎች አይተናል። እኛ በእነርሱ ፊት ልክ እንደ ፌንጣ (አንበጣ) ሆነን ነበር የታየነው እነርሱም እንደዚያ አድርገው ሳይመለከቱን አይቀሩም።" በማለት ፍርሃታቸውን ገለጹ (ዘኍ. 13፥28-33)።

ሁለቱ ሰላዮች ኢያሱና ካሌብ በእምነታቸው እንዳሰቡት ያቺን ማርና ወተት የምታፈሰውን ምድር ሲወርሱ እነዚያ ዐሥሩ ሰላዮች በምናባዊ ፍርሃታቸው ምክንያት ሌሎችንንም አስፈራርተው እነርሱም ተሸብረው በምድረ በዳ ቀርተዋል። እንዲህ ዓይነቱ ፍርሃት ያለበት ሰው ዘወትር ሰላሙ ይናጋል። ይከብደኛል፣ ያስፈራኛል፣ አልችልም በማለት ማግኘት የነበረበትን ያጣል፣ መሆን የነበረበትን ይስታል። ስል አንድ ጉዳይ ባሰበ ቁጥር በፍርሃት እና በድንጋጤ ይዋጣል ፍርሃቱም የውስጥ ስሜቱ የፈጠረው ምናባዊ እንጂ ከውጪ የመጣ (እውነተኛ) አይደለም።

እግዚአብሔርን የሚፈራ እና በእግዚአብሔር የሚታመን ግን በራሱ ምናባዊ (የሌለ) ፍርሃትን አይፈጥርም። ብዙ አዋኪ አደጋዎች



እና አስቸጋሪ ችግሮች ቢከቡትም እንኳን አይፈራም ወይም አይሸበርም።

ፈሪሀ-እግዚአብሔር ያደረበት የእግዚአብሔር ሰው ጌታ እንደተናገረው በአሸዋ ላይ ሳይሆን በዐለት ላይ እንደታነጸ ቤት ጽኑዕ እና ጠንካራ ነው። ይህንንም የቅዱስ ጴጥሮስ በእስር ቤት ሳለ ያሳየውን የእምነት ጽናት ከሚገልጸው ታሪክ መረዳት እንችላለን።

ቅ/ጴጥሮስ በታሰረ ጊዜ (ወደ ወህኒ በተወረወረ ጊዜ) ንጉሥ ሔሮድስ ሊገድለው ወስኖ ነበር። ይሁን እንጂ ቅ/ጴጥሮስ በእግዚአብሔር ስለሚታመን በዚህ የእስሩ ሁኔታ አንዳች ፍርሃት አልነበረበትም።

ለዚህም ነው የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ጴጥሮስን ከተኛበት ከሁለት ወታደሮች መካከል ቀስቅሶ አነቃውና ከታሠረበት ሰንሰለት ፈታው ከዚያም ከሔሮድስ የሞት ውሳኔ የታደገው (የሐዋ. ሥራ 12፥6-7)።

ምናባዊ ፍርሃት ፈጽሞ በሌለ እና በማይደርስ ነገር አዕምሮን የሚሞላ እና የማሰብ ችሎታን ፈጽሞ የሚያሰናክል ነው። ስለዚህ ፈሪ ሰው ከምናባዊ ፍርሃቱ የተነሣ የሚያስበው እና የሚያጋጥመው ሁኔታ ሁሉ የተወሳሰበ እና መፍትሔ የለሽ ይሆንበታል።

ለምሳሌ አንድ ሰው ለጤና ምርመራ ወደ ሐኪም ዘንድ ሲሄድ በውስጡ በሽታ ኖረበትም አልኖረበትም በጣም ይፈራል። ከፍርሃቱም የተነሣ አሁን ኤድስ ቢገኝብኝስ? እንዴት እሆናለሁ? እሞታለሁ ማለት



www.ethiopianorthodox.org

መለኮታዊ አሠራር ስንነጋገር እግዚአብሔር በተፈጥሮ ሕግ የማይተዳደር እና በተወሰነ ቀመር የማይገዛ መሆኑን ማመን አመርቂ መልስ ነው። አሁን ግን ወደ ሁሉም ጥያቄ ና ምላሽ ዝርዝር ውስጥ አንገባም ምክንያቱም የዚህ መጽሐፍ አላማ ለሚያጠራጥረን እና ጥያቄ ለሆነብን ሁሉ መልስ ለመስጠት ሳይሆን ጥርጣሬ ስሜታዊ መታወክን እና ብኩንነትን እንደሚያስከትል ለመጠቆም ነው።

## ➢ ፍትወት

ፍትወት ሌላ ነገር ሳይሆን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነትን በተግባር ለመተርጐም የሚዳረግ ፍላጎት ወይም ስሜት ነው። በትክክለኛው መንገድ ከሆነ የሩካቤ ሥጋ ስሜት (ፍትወት) በራሱ መጥፎ አይደለም።

በጋብቻ ክልል ውስጥ ባል ከሚስቱ ሚስትም ከባሏ ጋር ሩካቤ ሥጋ ለማድረግ ቢፈልጉ ወይም ቢያደርጉ ኃጢአት አይሆንባቸውም። ሩካቤ ሥጋ ከጋብቻ ክልል ውጭ ሲያመራ ግን ኃጢአት ከመሆኑ በላይ ሱስ መሆን ይጀምራል። ስም አጠራሩም "ዝሙት" ይባላል። ከእንስሳት በተለየ መልኩ በዝሙት ኃጢአት የሚጠቃው ደግሞ ሰው ብቻ ነው። ከሌሎች ፍጡራን በይበልጥ የሰው አዕምሮ ኃይል እጅግ ያስደንቃልና።

የሴት ልጅ አስተያየቷ፣ አካሄዷ፣ አድራጎቷ እና ደምግባቷ አንድን ወንድ ቢማርከው በአዕምሮው ሌላ ትርጉም ይኖረዋል እንጂ ተፈጥሮዋን በማድነቅ ብቻ አይወሰንም። በአዕምሮው ውስጥ



የተፈጠረው ትርጉምም ፍትወት ይባላል (ማቴ. 5፥28)። የሰው ልጅ ፍትወት የሚቀሰቀስበት መንገድ በዚህም ብቻ አይገታም፣ ወንድ የሴትን ልጅ ማንኛውንም ዓይነት የሰውነት ክፍሏን አይደለም በአካል፣ ቤቱ በሰጣጠፋቸው ስዕሎች እና አልበሙ ውስጥ በሸነቃቀራቸው ፎቶዎች እንዲሁም በየማስታወቂያው ሰሌዳ ላይ ባለው ምስል አማካይነት ሲመለከት ሁሉ ፍትወቱ ይቀሰቀስበታል። ይህም የሰው ፍትወት የሚጠነሰሰው በአዕምሮው ውስጥ እንደሆነ ያረጋግጣል፣ አዕምሮ ደግሞ ፍትወትን በትክክል መተርጎምና አቅጣጫ ማስያዝ ሲያቅተው ሰላምን ያናጋል፣ ለዝሙት ኃጢአት ያጋልጣል።

አንድ ታዋቂ የሥነ ልቡና ምሁር "ለማከናወን የምንፈልገው ነገር ሁሉ የሚመነጨው ካለን የሩካቤ ሥጋ ፍትወት እና ታዋቂ ሰው ለመሆን ካለን ጉጉት ነው።" ሲሉ እንደገለጹት።

ፍትወት ሰላማችንን ከሚያናጉ እና ለኃጢአት ከሚያጋልጡን የሥጋ ምኞቶች አንዱ መንሥኤ መሆኑን አስቀድመን ተናገርን እንጂ ሰው እንዲሟላለት የሚፈልገው ሌሎችም ዓይነት የሥጋ ምኞቶች አሉ። ምኞቶቹም ማኅለቅት የሌላቸው እና መጠነ ሰፊ ናቸው።

የሰው ልጅ አንዱን ምኞቱን ሲያሳካ ተከታይ ምኞቱ ብቅ ማለት ይጀምራል። ወደደም ጠላም በመጀመሪያ ግን መሠረታዊ ፍላጎቱ ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ፣ ጤና እንዲሟላለት ይጥራል ከዚህ በኋላ ነው ሌላኛው የፍላጎት ዓይነቱ የሚገተለተለው።



www.ethiopianorthodox.org

ባለቤቷን ለትዳሩ ታማኝ እና ለፍቅሯ ተገዥ እንዳልሆነ አድርጋ ትገምተዋለች ይህም ግምቷ ቅናት፣ ጥርጣሬ፣ ምቀኝነት... ስለሚያስከትል ፍቅራቸው እንዲቀዘቅዝ ትዳራቸው እንዲናጋ መንስኤ ይሆናል። ይህንን ለምሣሌ አቀረብኩኝ እንጂ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የብዙ ባለትዳሮች ሁለትዮሽ (ኅብረት) ሞቶ ተቀብሮአል።

እኔ ግን ድካም በተሰማዎ ጊዜ ጥፋትና ስሕተት እንዳይፈጽሙ የምለግስዎ ምክር ቢኖር እነሆ፦

*ደከመው ኀለ ከማንም ጋር ቃለ ምልልስ እና እሰጥ አገባ አይጀምሩ፣ በተለይ ሐሳብ ግትሮች ከሆኑ እና በቀላሉ ሀሳብዎን ሊረዱ ከማይችሉ ይራቁ በዚህን ጊዜ የልብ ወዳጅዎ እንኳን ሊጠነቀቅልዎ የግድ ነው።*

በድካም ጊዜ፣ ለችግሮች መፍትሔ ለማግኘት አንዳንድ ጉዳዮችን ለማከናወን እና ጥያቄዎችን ለመመለስ መታተር ውጤቱ አመርቂ ስላልሆነ ሁሉንም ነገር ለሌላ ቀን ወይም ሰዓት ያዘዋውሩት።

ሲደክምዎት ለድካምዎ መፍትሔ ይሆን ዘንድ ትንሽ እንቅልፍ እና እረፍት ያስፈልግዎታል፣ ድካምን አስወግዶ ስሜታዊ እና አዕምሮአዊ መረጋጋትን ለመፍጠር ሌላኛው ዘዴ ደግሞ የደስታን እና የሀሴትን መንፈስ በህሊናዎት መፍጠር መቻል ነው።

ለመደሰት እና ለመሳቅ ብቻ ከመጽሔት፣ ከጋዜጣ፣ ከተረት መጻሕፍት ቁምነገር አዘል አስቂኝ ቀልዶችን እና ለዛ ያላቸው ወጎችን



ሁልጊዜ የሚያነቡ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ውስጣቸው በደስታ አፋቸው በሳቅ ስለተሞላ ከአስቃቂ ወሬዎች የተነሳ ስሜታዊ መታወክ አይገጥማቸውም ምክንያቱም ደስታ የሰው ልጅ ፍጹም መረጋጋት እንዲኖረው የሚያስችሉ ያስችላል።

አፉን በሳቅ፣ ውስጡን በደስታ የሞላ ሰው ስሜታዊና አዕምሮአዊ መረጋጋት አለው፤ ይህ ሰው በቀላሉ አይበሳጭም፣ ወይም ለጸብም አይጋበዝም ይልቁንም ጸብን ሁሉ ወደ ቀልድ ለመቀየር ይቻለዋል፣ ይቀይራል።

ቁጣን ወደ ሳቅ የመለወጥም ብቃት ስላለው የሚቆጣውን እና የሚበሳጭበትን ሰው እንኳ በሚመልስለተ ምላሽ በሳቅ ያንከተክተዋል ከዚህ በኋላ በመካከላቸው በቁጣና በብስጭት ፈንታ ሳቅና ሰላም ያነግሳል። በጥቅሉ የማንንም ክብር እና መብት ሳይነካ ጥርስን የሚያስገልጥ ውስጥን የሚያፍነከንክ አስቂኝ ሰውን ሁሉም ይወደዋል።

በማንኛውም ጊዜ፣ ቦታ እና ሁኔታ ከሰዎች ጋር ያለው መቀራረብ የሰመረ ነው። ብዙዎች ይህን አስቂኝ ገና ከንፈሮቹን ሲያንቀሳቅስ በማየታቸው ብቻ ይሥቃሉ፤ ምክንያቱም የሚያስፈነድቃቸው እና የሚያስደስታቸውን ቃላት እንደሚጥል አስቀድመው ይገምታሉና ገና ጎህ ሲቀድ በጠዋት ካገኙትማ ቀኑን ሙሉ ደስተኛ ሆነው ይውላሉ።

ይሁንና በአንጻሩ ግን መሳቅ የኃጢአት ስሜት እና ውጤት እንደሆነ የሚያስቡ አንዳንድ ሰዎች አይታጡም።



www.ethiopianorthodox.org

ለማረጋጋት ከእርስዎ ሌላ ለእርስዎ የሚቀርብ ስለሌለ ብስጭትዎን እና ቁጣዎን ገደብ ያበጁለት እና እራስዎን ያረጋጉ።

እስኪ ድንጋይ አንስተው ወደ አንድ ተራራ ቢወረውሩ ተራራ ካለበት ቦታ ይንቃነቃል? አይንቃነቅም፤ ነገር ግን ያንኑ ድንጋይ ወደ መስታወት ቢወረውሩት መስታወቱ በቀላሉ ተሰባብሮ ይደቃል። እርስዎም እንደ ተራራው ጽኑዕ እና ጠንካራ ይሁኑ እንጂ መስታወቱ በቀላሉ እንደተሰበረ በሆነ ባልሆነው አይቆጡ ወይም አይበሳጩ።

ጽኑዕ ጠንካራ፣ ትዕግስተኛ፣ ሰው አፍቃሪ እና ትሑት ከሆኑ ብዙ ተጽኖዎች ቢከብዎትም እንኳን ይቋቋሟቸዋል እንጂ አይቆጡም። የአጋጠመዎትን ችግሮች ከመፍታትዎ አልፈው ለችግሮችዎ እና ለመሰናክልዎ መንስኤ የሆኑ ሰዎችን ሲያነጋግሩ እንኳ በፈገግታ ይሆናል። ፈገግታ ደግሞ የቁጣ ስሜት ሳይሆን የመረጋጋት ውጤት ነው።

ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ "ምንም ያህል ብትቆጡ ኃጢአት አትሥሩ" እንዳለው የሚቆጡበት አጋጣሚ ቢፈጠርና ቢቆጡም ቁጣዎ ከፍቅር ባኮ ውስጥ የወጣ እና በፍቅር የተለወሰ ስለሚሆን ለብዙዎች ሕይወት መታነጽ እንጂ መባዘን ምክንያት አይሆንም።

ምክንያቱም ቁጣ ሰዎችን ለጥፋት እና ለኃጢአት የሚያጋልጠው ቂም በቀልን፣ ጥላቻን እና የመሳሰሉትን ያዘለ ከሆነና ገደብ የለቀቀ ሲሆን ብቻ ነው። ለጤና ችግር እና ላለመረጋጋት እንዳይጋለጡ ቁጣዎ ገደብ የለቀቀ አይሁን።



◆ *ውጫዊ መንሥኤዎች*

ለስሜታዊ መታወክ፣ ለአዕምሮአዊ ብኩንነት እና ለአካላዊ አለመረጋጋት ውጫዊ መንሥኤዎች ብዙ ናቸው። አንድ መንፈሳዊ (ጽኑዕ) ሰው ግን በኋላ በትንታኔው እንደማብራራው እነዚህን ሁሉ ውጫዊ መንስኤዎች ማስወገድ እና ማሸነፍ ይቻለዋል።

አሁን በጣም አስፈላጊ የምንላቸው እና የምንዘረዝራቸው ከአካላት፣ ከስሜት ሕዋሳት፣ ከአዕምሮ፣ ከመንፈስ እና ከነፍስ ጋር ቁርኝት ያላቸውን ብቻ ነው።

ሀ) ስሜታዊ መታወክ፣ አዕምሮአዊ ብኩንነት እና አካላዊ አለመረጋጋት የሚያስከትሉ ጎልቶ መሳፍርት ምክንያቶች አሉ። ብዙዎቹ ምክንያቶች ከመኖሪያ ቤታችን እና ከምንኖርበት አካባቢ ጋር የተያያዙ ናቸው።

እነርሱም፡-
1. ጩኸት
2. ብርሃን
3. ቀለሞች
4. ማሽኖች

የመሳሰሉት ናቸው።



www.ethiopianorthodox.org

የሚስተናገደው ሁካታ ምንድነው? ሰውስ እንደዚህ አይነት ሁካታ ውስጥ ለምን ይኖራል? የሰው ልጅ ተረጋግቶ የሰላምና የፍቅር አየርን እየተነፈሰ መኖር የሚችልበት ጊዜስ መች ይሆን? ሲሉ መገረማቸውን በጥያቄ ይገልጻሉ።

በመሰረቱ የሰው ልጅ እኛ የምንኖረውን የኑሮ ሥርዐት የራሱ ካላደረገና የምናመልከውን አምላክ ካላመለከ መቼውም ቢሆን ተረጋግቶ መኖር ስለሚያቅተው በሁካታ ውስጥ ባለው ኑሮ የሕይወትን ጣዕምና ትርጉም ሊረዳ አይችልም። ምክንያቱም ሰላም እና ጸጥታ ሰማያዊ ኑሮን የምንኖርበት የሕይወት መንገድ ነው ሲሉ አማራጭ የሌለው መልስ ይሰጣሉ። መልሳቸውም በምድር ላይ የሚኖረው የሰው ልጅ ሰላሙ መናጋቱ እና በሁካታ ውስጥ የመኖሩ ዋነኛ መንሥኤ ሕገ እግዚአብሔርን አለመጠበቅ መሆኑን ያሳያል።

4. ሕገ እግዚአብሔርን ለመጠበቅ ሁካታን እና ጫጫታን ለመሸሽ ሲሉ ብቻ ብዙዎች የከተማ ነዋሪዎች ሙዚቃ ቤቶች፣ ወፍጮ ቤቶች፣ ተሽከርካሪዎች ፋብሪካዎች እና የንግድ ድርጅቶች ካሉበት እና ሕዝብ ከሚበዛበት ከደመቀ ከተማ ይልቅ ለመኖሪያ ቤታቸው በከተማ ዳርቻዎች ጸጥ ረጭ ያለ ቦታን ይመርጣሉ።

ለምሳሌ የለንደን ከተማ ሕዝብ ከ12 ሚሊዮን አልፎአል በዚህም ሳቢያ ብዙዎች የለንደንን ከተማ እየለቀቁ ከከተማው ውጪ "ሱብሪያ" በተባለ ቦታ መኖሪያቸውን እየመሠረቱ ነው።



5. አንዳንድ ከተሞች ደግሞ በከተማው ውስጥ ሰላም እና ጸጥታ ለማስፈን ጭንቀት፣ ሁከት እና አለመረጋጋትን ለማስወገድ ለነዋሪዎቻቸው ሕግና ደንብ አውጥተዋል። ይኸውም ሕግ ነዋሪዎች ለመኖሪያ ቤት መሥሪያ የተመሩትን ቦታ ድርጅቶችን እንዳይከፍቱባቸው እና ትልልቅ የንግድ ሕንጻዎችን እንዳይሠሩ ያግዳል።

በሌሎች ከተሞች ያለው ሕግ ደግሞ አንድ ሰው ለመኖሪያ ቤት የተመራውን ቦታ አንድ ሦስተኛውን ተጠቅሞ መኖሪያ ቤት እንዲሠራ እና ቀሪውን ቦታ የአትክልት እና የመናፈሻ ሥፍራ እንዲያደርግ ብቻ ይፈቅዳል።

ይህም የመኖሪያ ቤቶች ከፋብሪካዎች፣ ከንግድ ድርጅቶች ርቀው በተመቻቸ ስፍራ መሠራታቸው እና በውስጣቸውም ቀልብን የሚስብ፣ ዐይንን የሚማርክ፣ እና ስሜትን አድሶ ሰላምን የሚሰጥ የአትክልት እና የመናፈሻ ሥፍራ መደረጉ ለሁከታችን መፍትሔ መሆኑን ያረጋግጣል።

ይሁንና በአሁኑ ወቅት ከነዋሪዎች ብዛት አንጻር ተስማሚ፣ ምቹ እና ጸጥታ የሰፈነበት የመኖሪያ ቤት ማግኘት ከጥቂት ባለጸጎች እና ሰላም ወዳዶች በስተቀር ለብዙዎች በጣም ይከብዳል።

6. ይህንንም ችግር ለመቅረፍ አንዳንድ ከተሞች ለማኅበረሰቡ ጠቃሚ የሆኑ የመናፈሻ ቦታዎችን አዘጋጅተዋል። ይሁን እንጂ እነዚህ



www.ethiopianorthodox.org

ነፋስ ይመስላል። ይህ ሰው ዐይኑ ትዕቢተኛ፣ ምላሱ ሐሰተኛ፣ ልቡ ተንኮለኛ ነው። በአካሄዱም ከላባ እና በአነጋገሩም ወሽካታ ነው። ፀጥቅሉ በመላ አድራጎቱ እግዚአብሔር የተለየው ጸብ ጫሪ እና ሁከት ፈጣሪ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሌለበት ዕውቀቱ፣ ሀብቱ፣ ትጋቱ እና ማንኛውም ድርጊቱ ባዶ እና ከንቱ ነውና።

ለምሳሌ አንዳንድ ሰባኪዎች መስበክ ማለት መጮህ፣ መስበክ ማለት መወራጨት እና በመንፈስ ቅዱስ የሰከረ መስሎ መታየት ይመስላቸዋል።

ስለዚህም በሚሰብኩበት ጊዜ ዛር ከዚህ እዚያ ከዚያ እዚህ እያሉ ወዲያ እና ወዲህ ይወናጨፋሉ። እራሳቸውንም ፍጹም በማድረግ የሕዝቡን ኃጢአት ብቻ እየተናገሩ ይበሳጫሉ። በስብከታቸውም እግዚአብሔርን መሐሪነት ሳይሆን ጨካኝነት የእግዚአብሔርን ፍቅር ሳይሆን ጥላቻን ይሰብካሉ። ይኸውም ለምሳሌ በኃጢአታችሁ ምክንያት ሰማይ እሳት ቋጥሮአል፣ ከዚህን ቀን እስከዚህ ቀን ዝናም ይቆማል፣ እያሉ መጽሐፍ ቅዱስን ስበብ በማድረግ የራሳቸውን የኑሮ ዘዴ ይሰብካሉ። በዚህ ዓይነቱ ስብከትም ታዳሚዎች ተስፋ ቆርጠው እና ተበሳጭተው የእግዚአብሔርን ቃል የሰሙ ሳይሆን አስፈሪ እና አስደንጋጭ ትርዒት አይተው የተመለሱ ያህል ይጨንቃቸዋል። ስብከቱም ከተፈጸበት ሲያባንናቸው በእውናቸው ሲያውካቸው ይታያል። ይህ ዓይነቱ ስብከት ነፍሳትን የሚያስበረግግ እንጂ የሚያረጋጋ አይደለም።



ምን አልባት ብዙ ሰዎች የዚህ አይነት ስብከትን በሚሰብክ ሰባኪ ስሜታዊ እና አካላዊ እንቅስቃሴ ብቻ ይማረኩ ይሆናል። የቋንቋ አጠቃቀሙን፣ የዓረፍተ ነገር ቅንብሩን እና የቃላት አሰካኩንም ያደንቁለታል። ይሁን እንጂ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ የማረካቸውን እና በውስጣቸው የተሰማቸውን ውጤት ያጡታል።

ሰባኪውም የሚናገራቸው ቃላት የሸመደዳቸው እና ያጠናቸው እንጂ ከሕይወቱ እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የተስማሙ አይደሉም። ስለሆነም ምን እንደተናገረ ምን እንደሚናገር ለሰሚዎቹ ብቻ ሳይሆን ለራሱም አይገባውም።

ትክክለኛ ሰባኪ ግን በእግዚአብሔር አጋዥነት ታዳሚዎቹን በመንፈሳዊነቱ እና በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቱ አማካይነት ሰብኮ ያሳምናቸዋል። ይኸውም በመንፈስ ቅዱስ ምሪት እንጂ በራስ ስሜት በመስከር እና ገደብ የለቀቀ አካላዊ እንቅስቃሴን በመጠቀም አይደለም። ትክክለኛ ሰባኪ በስብከቱ እግዚአብሔር ዓለሙን እንዲሁ እንደወደደ እና አንድያ ልጁን እንደሰጠን በማብራራት እግዚአብሔር ለሰዎች ያለውን ፍቅር፣ መሐሪነት እና ይቅር ባይነት ይገልጻል።

ስብከቱም ሁል ጊዜ በሰሚዎች የልብ ሰሌዳ የተከተበ እና የተተከለ ይሆናል። ውጤቱም በእውናቸው ይቅርና በሕልማቸው አይረሱትም። ለአጭር ጊዜ በአካለ ሥጋም ሊረሱት ይቅርና በወዲያኛውም ዓለም በአካለ ነፍስም ሆነው ዝንተ ዓለም አይረሱትም።



www.ethiopianorthodox.org

መስራት እንዳለበት ስለሚያውጠነጥን እና ኃጢአትንም ከሰራ በኋላ በፍርሃት በስጋት በጸጸት ስለሚከበብ ኃጢአትን ከማድረጉ በፊትም ሆነ ኃጢአትን ከሠራ በኋላ ሰላም የለውምና (ኢሳ. 48፥22)።

የቃየን የሕይወት ጉዞ እና የቃየን ዝርያ የላሜህ የሕይወት ታሪክ ለዚህ ዋና ተምሳሌቶች ይሆኑናል። ይህቺ የምንኖርባት ምድር እንኳን ፍቅር፣ ሰላም እና ደስታን የተነጠቀችበት እና በምትኩ ሁከት አለመረጋጋት የነገሠባት አንዱ (ምክንያት) የቃየን ኃጢአት የተመረኮዘ ነው።

ቃየን ከገነት ውጪ የተወለደ እና ለሚኖርባት ምድርም ሆነ ለወላጆቹ ለአዳምና ሔዋን የበኩር ልጅ ነው።

ይህ የበኩር ልጅ ቃየንም በታናሽ ወንድሙ በአቤል ቀናበት፣ ቅናቱም ወደ መግደል አድጎ ወንድሙን አቤልን ገደለው።

ቃየንም ወንድሙን ከገደለ በኋላ እስከ ዕለተ ሞቱ ተቅበዝባዥ፣ ዘዋሪ፣ ኮብላይ፣ ፈሪ እና ጭንቀታም ሆነ። የሚያስፈራው እና የሚያውከው የወንድሙን የአቤልን አድራሻ የጠየቀው እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን የሚያየው ሰው ሁሉ ነበር (ዘፍ. 4፥12-14)።

ጭንቀት ፍርሃት፣ ስጋት እና ግራመጋባት ሥነ ልቡናዊ ተጽእኖዎች ሰላሙን ነሱት፣ እርሱም እነዚህን ሥነ-ልቡናዊ ተጽዕኖዎች ለማኅበረ ሰቡ ያስተዋወቀ ቀዳሚ ሰው ነው።



ጭንቀታምነቱ እና ፍርሃቱም ባለበት ማኅበረ ሰብ ሁሉ በእጅጉ ታወቀ። የእርሱም ዋይታ "ኃጢአቴ ልሸከማት የማልችላት ታላቅ ናት የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል" የሚል ነበር (ዘፍ. 4፥13-14)።

የቃየን ነፍሰ-ገዳይ መሆን በእርሱ ላይ ብቻ መታወክን ያስከተለ ሳይሆን ኋላ ኋላ በምድራችን ላይ ለተከሰቱትና ዓለም ሰላምን ሽቶ ሰላምን ላጣባት መረጋጋትን ፈልጎ ሁከትን ላስከተለባት ጦርነቶች መቅድሞም ሆነ።

በቃየን በኩል ከአዳም ሰባተኛ ትውልድ የሆነው እና ሁለት ሚስት ያገባው የቃየን ዝርያ ላሜህም እንዲሁ ነፍስ ገዳይ እና ሕግ አፍራሽ ነበር።

እርሱም ለሁለቱ ሚስቶቹ ኃጢአቱን ሲናገር "እናንተ የላሜህ ሚስቶች ቃሌን ስሙ፣ ነገሬን አድምጡ እኔ ጎልማሳውን ለቁስሌ ብላቴናውንም ለመዋጋቴ ገድዬዋለሁ፣ ቃየንን ሰባት እጥፍ ይበቀሉታል፣ ላሜህን ግን ሰባ ሰባት እጥፍ።" ሲል አለመረጋጋቱን ያስከተለበትን ሰቆቃ አዘል ኑዛዜ ተናዟል (ዘፍ. 4፥23-24)።

ይህም ሰቆቃ አዘል ኑዛዜ ምድር ቂመኞችን በቀለኞችን እና ጭንቀታሞችን እንደያዘች፣ ዓለምም በክፋት እንደሰጠመች እና በኃጢአተኞች የራሷንም ሰላም እንዳጣች ያመላክታል።



www.ethiopianorthodox.org

ኃጢአተኛ በዚህ ዓለም በሚኖርበት ሥጋዊ ኑሮ ብቻ ሳይሆን ከሞት በኋላ ስላለው ዘላለማዊ ኑሮ ሲያስብም ይታወካል። በዳግም ምጽአት የሚደርስበትን የቅጣት ፍርድ ሲያብሰለስል ይጨነቃል።

በሕገ-እግዚአብሔር የሚኀገዝ መንፈሳዊ ሰው ግን "አሁንም ልጆች ሆይ በሚገለጥበት ጊዜ እምነት እንዲሆንልን በመምጣቱም በእግዚአብሔር ፊት እንዳናፍር በእርሱ ኑሩ" የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልእክት ዘወትር ስለሚያነብ በተስፋ ብቻ ደስተኛ ነው።

በእርግጥ ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ "በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው" ሲል እንደነገረን ኃጢአታችንን ላልተናዘዝን እና በኃጢአታችን ንስሐ ላልገባን ከሞት በኋላ ያለው ዘላለማዊ ኑሮ ሕይወት ሳይሆን ሞት ይሆንብናል።

ኃጢአቱን የተናዘዘ እና ንስሐ የገባ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ጥሩ ግንኙነት ስላለው ከቅ/ጳውሎስ ጋር "ልሄድ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና" (ፊል. 1፥23) ይላል። ንስሐ ያልገባ ኃጢአቱን ያልተናዘዘ ሰው ግን ዘወትር በሕግ አፍራሽነቱ በእምነት አልባነቱ ከእግዚአብሔር አሠራር ጋር ይቃረናል።

በዚህም ምክንያት ስለሞት፣ ከሞት በኋላ ስላለው ዘላለማዊ ኑሮ፣ ስለፍርድ፣ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት ሲነገር ነፍሱ በጣም ትታወካለች።



እንደዚህ ዓይነት ርዕስ ያላቸውን ወሬዎች ላለመስማት ይወስናል ነገር ግን እነዚህን ዓይነት ወሬዎች ባይሰማም እንኳን በውስጡ ኃጢአቱ የቀረጸበት ፍርሃት እና ሥጋት ያስጨንቀዋል። ስለዚህ በኃጢአት ላለመታወክ መፍትሔው ኃጢአትን መናዘዝ ስለሆነ ዛሬውኑ ንስሐ ገብተው ኃጢአትዎን ይናዘዙ እና በሕይወት ይኑሩ።



www.ethiopianorthodox.org

15. ችግሮች ከአቅም በላይ ሆነው ቢወሳሰቡ እና መፍትሔ ቢያጡላቸው እንኳን አይጨነቁ። ስላምዎንም አያደፍርሱ፤ ነገር ግን ሐሳብዎን ሊገነዘብ ወደሚችለው ሰው ወይም ለችግርዎ መፍትሔ ሙያዊ ብቃት ወዳለው ባለሙያ በመሄድ ምክርን ይቀበሉ። በእውነትም ከምክሩ ለችግርዎ መፍትሔ እና የውስጥ ሰላምዎን የሚያድሱበት አዲስ ሐሳብ፣ ትክክለኛ አቅጣጫ እና የሕይወት መንገድ ያገኛሉ።

16. በኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ በምኞት አለመሳካት እና በሕይወት መሰላቸት አማካይነት ሰላሙን ያጣ ሰው የዚህችን ዓለም ውበት እና ጣዕም የናቁትን የመናንያንን ታሪክ ቢያውቅ ወይም የምናኔ መንፈስ በህሊናው ቢያሳድር ፍጹም የተረጋጋ ሰላማዊ ይሆናል።

በእውነት እርስዎም ምኞትዎ ማለቂያ እና መቋጫ ባይኖርምም እንኳን ሁሉም ነገር ጊዜውን ጠብቆ ኃላፊ እና ረጋፊ መሆኑን ከተረዱ የዚህችንም ዓለም ማለፍ ከተቀበሉ ተረጋግተው እና ሰላም አግኝተው ለመኖር አያቅትዎትም።



www.ethiopianorthodox.org